Montgomery County Fire and Rescue Service
Community Risk Reduction • www.mcfrs.org/mcsafe • X @mcfrs

# የሻማ አጠቃቀም ደህንነት

ሻማዎች ሲታዩ የሚያምሩ ሊሆኑ ይችላሉ፣ ነገር ግን ለቤት ውስጥ እሳት መነሳት እና በቤት ውስጥ በሚነሳ እሳት ምክንያት ለሚከሰቱ ሞቶች መንስኤዎች ናቸው። ያስታውሱ፤ ሻማ ክፍት የሆነ የእሳት ነበልባል ነው፣ ይህም ማለት በቀላሉ ሊቃጠል የሚችል ማንኛውንም ነገር ሊያቃጥል ይችላል።

**"ሻማን በጥንቃቄ ይጠቀሙ"**

- ክፍሉን ለቀው ሲወጡ ወይም ወደ መኝታ ሲሄዱ ሁሉንም ሻማዎች ያጥፉ። በመኝታ ክፍል ውስጥ እና ሰዎች እንቅልፍ ሊወስዳቸው በሚችሉ ሌሎች ስፍራዎች ሻማዎችን ከመጠቀም ይቆጠቡ።
- ሻማዎችን ሊቃጠል ከሚችል ከማንኛውም ነገር ቢያንስ 1 ጫማ (30 ሴንቲሜትር) ያህል ያርቁ።

*በቤትዎ ውስጥ የእሳት ነበልባል የሌላቸውን ሻማዎችን መጠቀምን ያስቡበት።*
*እውነተኛ ሻማ ይመስላሉ እና እንደ እውነተኛ ሻማ ሽታ አላቸው።*

**ሻማዎችን የሚጠቀሙ ከሆነ፣ የሚከተሉትን ጥንቃቄዎች ያድርጉ...**

- ጠንካራ እና በቀላሉ የማይወድቁ የሻማ መያዣዎችን ይጠቀሙ።
- የሻማ መያዣዎችን በማይነቃነቅ እና በሌሎች እቃዎች ባልተጨናነቀ ቦታ ላይ ያስቀምጡ።
- ሻማዎችን በጥንቃቄ ያብሩ። ፀጉርዎን እና ማንኛውንም የተንጠለጠለ ልብስ ከእሳት ያርቁ።
- ሻማውን እስከታች ድረስ እስከሚያልቅ አያቃጥሉ፣ ወደ መያዣው በጣም ከመጠጋቱ በፊት ያጥፉት።
- በቤት ውስጥ ኦክሲጅን ጥቅም ላይ የሚውል ከሆነ ሻማ በጭራሽ እንዳይጠቀሙ።
- ባትሪዎች እና በባትሪ የሚሰራ መብራት፣ መብራት በሚጠፋበት  ጊዜ ለመጠቀም እንዲችሉ ያዘጋጁ። ሻማዎችን በጭራሽ አይጠቀሙ።

**ሻማዎች እና ልጆች**

የተለኮሰ ሻማ ባለው ክፍል ውስጥ ልጆችን ብቻቸውን አይተዉ። ክብሪቶችን እና ላይተሮችን ህጻናት በማይደርሱበት ከፍ ባለ እና በተቆለፈ ካቢኔት ውስጥ ያስቀምጡ።

**እውነታዎች**

- ዲሴምበር ወር በሻማ ምክኒያት የሚነሱ እሳቶች በብዛት የሚከሰቱበት ወር ነው።
- ከአንድ ሶስተኛ በላይ በሻማ ምክኒያት የሚከሰቱ እሳቶች ከመኝታ ክፍል ውስጥ የሚነሱ ናቸው።
- ከእያንዳንዱ አምስት በሻማ ምክኒያት የሚከሰቱ እሳቶች ውስጥ ሦስቱ የሚከሰቱት ተቀጣጣይ የሆኑ ነገሮች ሻማው ጋር በጣም ተጠግተው በመቀመጣቸው ነው።

ለነጻ የቤት ደህንነት ፍተሻ ወደ 311 ይደውሉ፣ www.mcfrs.org/mcsafe